
ABG21
መልካም ዕድል ለብሔራዊ ቡድናችን
የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ደስታ

# ማውጫ

# ጉዞ ወደ ሞሮኮ


## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ቀጣዩ ፈተና

የሶከር ኢትዮጵያው አብርሃም ገብረማርያም ወደ ሞሮኮው የአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ የሚደረገው የማጣሪያ ጉዞ ምን ሊመስል እንደሚችል በዚህ ቅድመ ዕይታ ያሳየናል።

# 'አዲሱ' የባሬቶ ስብስብ....

በእግርኳስ ድሎች እና ሽንፈቶች ወደ ታሪክ የሚለወጡበት ፍጥነት አስገራሚ ነው፡፡ ያለፉት ሁለት አመታትን በአንፃራዊ ስኬት ከተጓዘ በኋላ እየተንሸራተተ የመጣው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንም የዚህ አካል ከመሆን እና አለመሆን መስመር ላይ ቆሟል፡፡ አሁን 2012 ላይ ሳይሆን 2014 ላይ ነን፡፡ በሁለት የደርሶ መልስ ማጣርያ ጨዋታዎች ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፍ የማይታሰብ ነው፡፡ የያኔው አሰልጣኝ አሁን የሉም፡፡ ላለፉት 2 አስርት በሚልቁ አመታት ከኢትዮጵያ እግርኳስ ጋር የሚተዋወቁት ሰውነት ቢሻው ለቀው በኢትዮጵያ እግርኳስ የዜሮ አመት ልምድ ባላቸው አሰልጣኝ ተተክተዋል፡፡ ብሄራዊ ቡድናችን በአሁኑ ወቅት በፊፋ ወርሃዊ ደረጃ 112ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡ ምናልባት ይህ የመንሸራተታችን ምልክት መግለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገራት በተለየ የወዳጅነት ጨዋታዎች እና በርካታ ውድድሮች ላይ የማትሳተፍ በመሆኗ ደረጃው ያለንበትን ወቅታዊ ሁኔታ ላይገልጽ ይችላል፡፡ ዋልያዎቹ ባለፉት 8 ወራት (2014 ከገባ ወዲህ) ያከናወኑት በፊፋ ዕውቅና ያለው ጨዋታ ጥቂት መሆኑን ስንረዳ በጨዋታዎች ውጤት ፣ የተጋጣሚዎች የብቃት ደረጃ እና የአሸናፊነት ልኬት ላይ ተመስርቶ የሚወጣው የፊፋ ደረጃ መመዘኛ ላይሆን ይችላል ብለን መከራከር እንችላለን፡፡ ነገር ግን ቡድኑ አሁንም ጠንካራ ነው ማለት አይደለም፡፡ በቀላሉ የሚሸነፍ ፣ ግብ ማስቆጠር የሚከብደውና ከጨዋታ ጨዋታ ትልልቅ ድክመቶቹ ጎልተው የሚወጡበት ቡድን እየሆነ መጥቷል፡፡ ቡድኑ በሽግግር ላይ ይሆን? ብሄራዊ ቡድኑ በአዲስ አሰልጣኝ ስር አዲስ ጉዞ በመጀመሩ ሽግግር ላይ ነው ብለን ልንከራከር እንችላለን፡፡ ነገር ግን በቡድኑ አዲስ ፊት የሚባሉት አሰልጣኙ እና ጥቂት ተጫዋቾች እንጂ ሙሉ ቡድኑ አይደለም፡፡ ምናልባትም አሰልጣኙ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንን ላለፉት ጥቂት አመታት በቅርበት መከታተላቸው አጠራጣሪ መሆኑ ቡድኑን በአሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ዘይቤ ከመምራት ይልቅ ወደ ራሳቸው ዘይቤ ለመውሰድ ይሞክራሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

ተጨማሪ ለማንበብ ወደ ገፅ 3 ይሂዱ።









**2 የሶከር ኢትዮጵያ መልዕክት**
በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያው ቀደም ተከተል እና መደረገወ ስለሚገባቸው ነገሮች ኦምና ታደለ የሚለው ነገር አለ።

**6 የአፍሪካ ዋንጫ እውነታዎች**
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እስካሁን በተሳተፈባቸው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያዎች ያስመዘገባቸውን ውጤቶች ጨምሮ የተለያዩ እውነታዎች

**9 አልጄሪያ**
የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ተጋጣሚ የሆነው የአልጄሪያ ብሔራዊ ቡድን ዳሰሳ

**11 ማላዊ**
በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያው የኢትዮጵያ ሁለተኛ ተጋጣሚ የሆነው የማላዊ ብሔራዊ ቡድን ዳሰሳ

**13 የዋሊያዎቹ ስብስብ**
አሰልጣኝ ማርያኖ ባሬቶ ለቀጣዮቹ ጨዋታዎች የጠሯቸው ተጫዋቾች እነማን ናቸው?

**17 ዋሊያዎቹ በምስሎች**
በባሬቶ ቡድን የመጨረሻው 24 ውስጥ የገቡ ተጫዋቾች ምስል ከክለቦቻቸው ጋር

ሶከር ኢትዮጵያ

Soccer Ethiopia, PO Box
25192/1000, Addis Ababa, Ethiopia
Tel: +251 -913-041-925
+251 -910-847-505
Email: info@soccerethiopia.com
Website:
www.soccerethiopia.com
Facebook: Soccer Ethiopia
Twitter: @soccerethiopia

የሶከር - ኢትዮጵያ ቡድን

ፀሐፊዎች

አብርሐም ገብረማሪያም
ኦምና ታደሰ
ሳሙኤል የሺዋስ

ለሶከር ኢትዮጵያ ፅሁፎችን ለመፃፍ ይፈልጋሉ?

የኢትዮጵያ እግር ኳስን ከልብ የሚወዱ፣ በቋሚነት የሚከታተሉ፣ በእግር ኳሳችን ዙሪያ የተለያዩ ፅሁፎችን የሚፅፉ እንዲሁም ፅሁፎችዎ በሶከር ኢትዮጵያ እንዲወጡ የሚፈልጉ ከሆነ ከታች በተመለከተው የኢሜይል አድራሻ ይፃፉልን። ከህትመታችን ጋር የሚሄዱ ፅሁፎችን፣ ምስሎችን፣ ቪድዮዎችን ተቀብለን በቀጣይ እትሞች እናካትታለን።

ኢሜይል፡ info@soccerethiopia.net

ይጎብኙ፡ www.soccerethiopia.net

አብግ 21 ኮምዩኒኬሽን እና ማስታወቂያ
21
ABG 21 COMMUNICATION & ADVERT

# ጊዜው አሁን ነው...



ዋልያዎቹ ባለፉት ሁለት አመታት ካስመዘገቡት አንፃራዊ ስኬት በኋላ በአዲስ አሰልጣኝ አዲስ ፈተና ሊጋፈጡ ተዘጋጅተዋል፡፡ ቡድኑ በአሰልጣኝ ማርያኖ ባሬቶ እየተመራ ክረምቱን በዝግጅት እያሳለፈ ነው፡፡ በብራዚል እና ሀዋሳ ተቀምጦ ያሳለፈውን የዝግጅት ጊዜ ጨምሮ ከአንጎላ ብሄራዊ ቡድን ጋር የአቋም መለኪያ ጨዋታ አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ ከፊታችን የተደቀነው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያ ፈተና ነው፡፡

ቡድኑ ተጫዋቾቹን ቀደም ብሎ በመምረጡ አሁን ስለ ምርጫ ውዝግብ የምንቀመጥበት ወቅት አይደለም፡፡ ፌዴሬሽኑ አሁንም በርካታ ስህተቶች ቢሰራም በጎ በጎውን እያሰብን ከፌዴሬሽኑ ጎን የመቆምያ ጊዜያችን አሁን ነው፡፡ ለአመታት ወደኋላ ያስቀሩንን የክለብ ስሜቶች እና የግለሰብ ሽኩቻዎችን ትተን ዋልያዎቹን በሚገባ ልንደግፍ ይገባል፡፡ ፌዴሬሽኑም ከሌሎች ከብሄራዊ ቡድኑ በታች ካሉ ጉዳዮች በላቀ ዋልያዎቹ ላይ ትኩረት የማድረጊያው ጊዜም አሁን ነው፡፡

ሶከር ኢትዮጵያ ፌዴሬሽኑ ለወትሮው ብሄራዊ ቡድኑ ጨዋታ ሲኖረው የሚሰጠውን ቅጥ ያጣ ትኩረት ይቀጥልበት እያለች አይደለም፡፡ ለብሄራዊ ቡድን ትኩረት በመስጠት ሰበብ አላግባብ የሚባክነው ጊዜ እና ገንዘብ ግን መልክ ሊይዝ ይገባል የሚል አቋም አለን፡፡ ፌዴሬሽኑ የእግር ኳሳችን የበላይ አካል እንደመሆኑ መጠን በሁሉም እግርኳሳዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን ማሳረፉን በብሄራዊ ቡድኑ ጨዋታ እለትም ሳይቀር መዘንጋት የለበትም፡፡

ለጨዋታው የቀረው ጊዜ አጭር በመሆኑ ጊዜው ረፍዷል ብለን መዘናጋት አይገባንም፡፡ ሁልጊዜም ዝግጅት ማለት ልምምድ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አስተዳደራዊ እና አጠቃላይ የሜዳ ውጪ ዝግጅትም ጭምር ነው፡፡ ፌዴሬሽኑ ለአመታት የህዝቡ ምሬት የሆነውን የትኬት አሰራር በጊዜያዊነትም ቢሆን መላ መፈየድ ይኖርበታል፡፡ ብሄራዊ ቡድኑ ጨዋታ በሚኖርበት ጊዜ ከአንድ ቀን ቀደም ብሎ መሰለፍን ብሎም በስቴድየም ዙርያ ማደርን የለመደው እግርኳስ አፍቃሪ ከእንግልት ለማዳን ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየጎላ የመጣው የፓስፖርት እና የተጫዋቾች ምዝገባ ስህተትም አሁን ሊደገም አይገባውም፡፡

ፌዴሬሽኑ ለችግሮች ሁሉ ፈጣን ምላሾች የሚሰጥበት ወቅት ላይ ብንገኝም ለዘለቄታው ማሰብንም ሊዘነጋው አይገባም፡፡ የማጣርያው ጉዞ ለወራት የሚዘልቅ በመሆኑ ተደጋጋሚ ችግሮችን ከመሰረቱ የመፍታት ኃላፊነት አለበት፡፡

ጮቤ ያስረገጡን ያለፉት ሁለት አመታት ውጤቶች በማጣርያውም እንዲደገሙ ከአሰልጣኙ ጎን መቆማችን የግድ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ትዕግስት፣ እምነት መጣል እና የማያቋርጥ ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡ አሰልጣኙ በኢትዮጵያ ጥቂት ጊዜያት እንደመቆየታቸው የእግር ኳስ ስርአታችንን፣የተጫዋቾቻችንን ባህርይ፣ የእግር ኳሱን አሰራር እና የደጋፊውን ባህርይ ተረድተውታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በአዲሱ አሰልጣኝ ላይ ከመጠን ያለፉ ትችቶች፣ ጣልቃ ገብነቶች እና ውጤታማ ባልሆኑበት ሰአት የሚሰነዘሩ የበዙ ተቃውሞዎችን የምናሰማ ከሆነ ከፍተኛ ወጪ ባወጣንባቸው አሰልጣኝ ከፍተኛ ኪሳራ ማስተናገዳችን አይቀርም፡፡

መልካም እድል ለብሄራዊ ቡድናችን

በዚህ መፅሄት ላይ የወጡ ፅሁፎች የሶከር ኢትዮጵያ ናቸው። እባክዎትን ፅሁፎቹን በሚጠቀሙበት ጊዜ ምንጭ መጥቀስዎን አይዘንጉ።

# አልጄሪያን ማሸነፍ ወሳኝ ነው



ሞሮኮ ለምታስተናግደው 30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታዎች ከመጪው ጳጉሜ ወር ጀምሮ ይደረጋሉ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫን የምታስተናግደው ሰሜን አፍሪካዊቷ ሞሮኮ ዝግጅቷን ከሞላ ጎደል አጠናቃለች፤ በአራት ከተሞቿም የአህጉሪን ትልቅ ውድድር ታስተናግዳለች፡፡ ዋና ከተማዋ ራባት፣ የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮናን ከሳምንት በፊት በተሳካ ሁኔታ ያስተናገደችው ማራካሽ፣ አጋድር እና ታንጊር ዝግጅታቸውን አጠናቀቀው እንግዶችን በመጠባበቅ ላይ ናቸው፡፡ የካዛብላንካው ስታዲየም እንደ አማራጭ ሜዳነት ተይዟል፡፡ የምድብ ድልድሉ የማጣርያ ጨዋታዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ኖቬምበር 26 በራባት ከተማ የሚካሄድ ሲሆን በጃንዋሪ 2015 ውድድሩ ይጀምራል፡፡ በማጣርያው ኢትዮጵያን ጨምሮ 21 የተሻለ ደረጃ ያላቸው ቡድኖች ቀጥታ ወደ ምድብ ማጣሪያው በቀጥታ አልፈዋል፡፡ የተቀሩት 26 ቡድኖች ደግሞ ከ2 የቅድመ-ማጣሪያ ዙሮች በኋላ ምድቡን ተቀላቅለዋል፡፡ በምድብ ሁለት ከአልጄሪያ፣ ማሊ እና ማላዊ ጋር የተደለደለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንም የማጣሪያ ጨዋታውን ከጳጉሜ 2 ጀምሮ ያደርጋል፡፡ በመጀመሪያ ጨዋታው ከአልጄሪያ ብሄራዊቡድን ጋር አዲስ አበባ ላይ የሚገናኘው ቡድኑ በቀጣይነትም ማላዊን ከሜዳው ውጪ ይገጥማል፡፡

> “እነሱ ለረጅም ጊዜ ሲዘጋጁ አሳልፈው ሊሆን ይችላል፤ በርካታ በአውሮፓ ሊጎች የሚጫወቱ ተጫዋቾችም ሊኖሯቸው ይችላል። መርሳት የሌለብን ግን ወደ ሜዳ ስንገባ በሁለታችንም ቡድን ውስጥ ያሉት እኩል 11 ተጫዋቾች እንደሆኑ ነው።”
>
> *አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ከደቡብ አፍሪካው ጨዋታ በፊት የተናገሩት*

ከ31 አመታት በኋላ በ29ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የተሳተፈው ብሄራዊ ቡድናችን በአዲስ አሰልጣኝ ቀጣዩን የአፍሪካ ዋንጫ እያለመ ጉዞ ጀምሯል፡፡ ከ2014 ያልተሳካ የቻን ውድድር በኋላ ከአሰልጣኝነታቸው መንበር የተነሱትን ሰውነት ቢሻውን ተክተው የብሄራዊ ቡድኑ አሰልጣኝ የሆኑት ፓርቹጋላዊው ማሪያኖ ባሬቶ የተጫዋች ምርጫ አድርገው ወደ ዝግጅት ከገቡ ወራት ተቆጥረዋል፡፡ ከሀዋሳ የሳምንታት ቆይታ በኋላ ዋሊያዎቹ ወደ ሉዋንዳ አቅንተው ከአንጎላ ጋር የወዳጅነት ጨዋታ አድርገዋል፡፡ ወደ ብራዚል አቅንተውም ከ5 ክለቦች ጋር የአቋም መለኪያ ጨዋታ አድርገዋል፡፡ ምንም እንኳን ዋሊያዎቹ ጨዋታ ማሸነፍ ባይችሉም ለጨዋታ ዝግጁ ከመሆን አንፃር ጠቃሚ ጉዞ አድርገው ተመልሰዋል፡፡

ሰውነት ቢሻው ሲመሩት የነበረው ብሄራዊ ቡድኑ ደቡብ አፍሪካ ባዘጋጀችው የአፍሪካ ዋንጫ ቤኒን እና ምስራቅ አፍሪካዊቷን ሱዳን አሸንፎ ቢያልፍም በደቡብ አፍሪካው የአፍሪካ ዋንጫ ያልተሳካ ጉዞ አድርጓል፡፡ ከደቡብ አፍሪካ የአፍሪካ ዋንጫ መልስ በምስራቅ አፍሪካ አገሮች ውድድር ላይ የተሳተፈው ብሄራዊ ቡድኑ በሩብ ፍፃሜ በሱዳን ተሸንፎ ከውድድር ውጪ ሆኗል፡፡ በቻንም አንድም ግብ ሳያስቆጥር ከምድብ ተሰናብቷል፡፡ ይህንን ተከትሎም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻውን አሰናብቶ በምትካቸው ፖርቹጋላዊውን ማሪያኖ ባሬቶን ሹሟል፡፡ ማሪያኖ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ በጣት የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታዎችን መመልከት የቻሉ ሲሆን ከቴክኒክ ኮሚቴው ጋር በመሆንም የተጫዋች ምርጫ አድርገዋል፡፡ በውጤት ደረጃ የሚመጣ ለውጥ ካለ ወደፊት የምናየው ቢሆንም ዋሊያዎቹ የተሻለ [illegible]

አልጄሪያ በቀድሞ የሉርዮ አሰልጣኝ ዮሀን ጎርከፍ እየተመራች አዲስ አበባን ትጎበኛለች፡፡ አልጄርያን ለውጤት ያበቋት ቦስኒያዊው ሃሚድ ሳሊልሆድዚችን ተክተው መንበረ ስልጣኑን የተረከቡት ጎርኩፍ ለአፍሪካ እግርኳስ አዲስ ቢሆኑም ጠንካራ ቡድን ይሰራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ አልጄሪያ አብዛኛው የቡድኗ ስብስብ የብራዚሉ አለም ዋንጫ ላይ የተካፈለው ነው፡፡ ማሊም በአውሮፓ የእግርኳስ ህይወታቸውን በማሳለፍ ላይ የሚገኙት ተጫዋቾች ይዛ ወደ ውድድሩ ትቀርባለች፡፡ በትልቅ ደረጃ ላይ የሚጫወቱ ተጫዋቾች እምብዛም የሌሏት ማላዊ ከምድቡ ለማለፍ ዝቅተኛ ግምት ተሰጥቷታል፡፡

ከምድቡ አንደኛ እና ሁለተኛ ሆነው የሚጨርሱ ቡድኖች ቀጥታ ለሞሮኮው የአፍሪካ ዋንጫ የሚያልፉ ይሆናል፡፡ ከምድብ ለማለፍ በሜዳ ላይ የሚደረግ ጨዋታን ማሸነፍ ግድ ይላል፡፡ የማጣሪያ ጨዋታዎቹ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ የሚጠናቀቅ በመሆኑ በሜዳ ላይ የሚዘገቡ ውጤቶች ወሳኝ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንም በተለይ የምድቡ ጠንካራ ቡድን ከሆነው አልጄሪያ ጋር አዲስ አበባ ላይ የሚያደርገው ጨዋታን ማሸነፍ ወሳኝ ነው፡፡

የማሪያኖ ባሬቶ ቡድን ጥረቱ ሰምሮ ቀጣዩ ጨዋታዎችን አሸንፎ በሃገራችን ጎዳናዎች ላይ ህዝባችን ደስታውን ሲገልፅ ማየት የሶከር ኢትዮጵያ ምኞት ነው፡፡

መልካም ዕድል ለዋሊያዎቹ



# ጉዞ ወደ ሞሮኮ - ክፍል 1

**የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን መድረሻውን የሞሮኮውን የአፍሪካ ዋንጫ ለማድረግ የማጣርያ ጨዋታውን ሊጀምር ተቃርቧል። በመጨረሻው ውድድር የተካፈለችው ሃገር በድጋሚ በአፍሪካ ትልቁ ውድድር በድጋሚ የመታየት ጫና አለባት፡፡ ቀጣዩ ፅሁፍም ዋልያዎቹን የሞሮኮ ጉዞ - ክፍል አንድ ለመዳሰስ ይሞክራል።**

በእግርኳስ ድሎች እና ሽንፈቶች ወደ ታሪክ የሚለወጡበት ፍጥነት አስገራሚ ነው፡፡ ያለፉት ሁለት አመታትን በአንፃራዊ ስኬት ከተጓዘ በኋላ እየተንሸራተተ የመጣው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንም የዚህ አካል ከመሆን እና አለመሆን መስመር ላይ ቆሟል፡፡ አሁን 2012 ላይ ሳይሆን 2014 ላይ ነን፡፡ በሁለት የደርሶ መልስ ማጣርያ ጨዋታዎች ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፍ የማይታሰብ ነው፡፡ የያኔው አሰልጣኝ አሁን የሉም፡፡ ባለፉት 2 አስርት በሚልቁ አመታት ከኢትዮጵያ እግርኳስ ጋር የሚተዋወቁት ሰውነት ቢሻው ለቀው በኢትዮጵያ እግርኳስ የዜሮ አመት ልምድ ባላቸው አሰልጣኝ ተተክተዋል፡፡ ብሄራዊ ቡድናችን በአሁኑ ወቅት በፊፋ ወርሃዊ ደረጃ 112ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡ ምናልባት ይህ የመንሸራተታችን ምልክት መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገራት በተለየ የወዳጅነት ጨዋታዎች እና በርካታ ውድድሮች ላይ የማትሳተፍ በመሆኗ ደረጃው ያለንበትን ወቅታዊ ሁኔታ ላይገልጽ ይችላል፡፡ ዋልያዎቹ ባለፉት 8 ወራት (2014 ከገባ ወዲህ) ያከናወኑት በፊፋ ዕውቅና ያለው ጨዋታ ጥቂት መሆኑን ስንረዳ በጨዋታዎች ውጤት ፣ የተጋጣሚዎች የብቃት ደረጃ እና የአሸናፊነት ልኬት ላይ ተመስርቶ የሚወጣው የፊፋ ደረጃ መመዘኛ ላይሆን ይችላል ብለን መከራከር እንችላለን፡፡ ነገር ግን ቡድኑ አሁንም ጠንካራ ነው ማለት አይደለም፡፡ በቀላሉ የሚሸነፍ ፣ ግብ ማስቆጠር የሚከብደውና ከጨዋታ ጨዋታ ትልልቅ ድክመቶቹ ጎልተው የሚወጡበት ቡድን እየሆነ መጥቷል፡፡ ቡድኑ በሽግግር ላይ ይሆን? ብሄራዊ ቡድኑ በአዲስ አሰልጣኝ ስር አዲስ ጉዞ በመጀመሩ ሽግግር ላይ ነው ብለን ልንከራከር እንችላለን፡፡ ነገር ግን በቡድኑ አዲስ ፊት የሚባሉት አሰልጣኙ እና ጥቂት ተጫዋቾች እንጂ ሙሉ ቡድኑ አይደለም፡፡ ምናልባትም አሰልጣኙ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንን ባለፉት ጥቂት አመታት በቅርበት መከታተላቸው አጠራጣሪ መሆኑ ቡድኑን በአሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ዘይቤ ከመምራት ይልቅ ወደ ራሳቸው ዘይቤ ለመውሰድ ይሞክራሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

አሰልጣኙ የራሳቸውን ፍልስፍና ተከትለው የቡድኑን አጨዋወት እና ቋሚ ተሰላፊዎች ለመወሰን ከሞከሩ ቡድኑን ወደራሳቸው ለማምጣት ጊዜያት ሊወስድባቸው ይችላል፡፡ በአፍሪካ ዋንጫው ማጣሪያ ከአልጄርያ እና ማላዊ ጋር ለሚደረጉት ጨዋታዎች ዝግጅት ከተመረጡት የመጨረሻዎቹ 30 ተጫዋቾች መካከል በአሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ስር ያልተጫወቱት ተጫዋቾች ከ20 አመት በታች ቡድኑ ያደጉት አንዳርጋቸው ፣ ዳዋ እና ናትናኤል ብቻ መሆናቸውም ልብ ይሏል፡፡

ብሄራዊ ቡድኑ 2006 ከገባ ወዲህ ያሸነፈው ጨዋታ ሁለት ብቻ ነው:: እነሱም በፊፋ እውቅና ያልሰጣት ዛንዚባርን እና አዲሷን ደቡብ ሱዳን በሴካፋ ውድድር ያሸነፋት ነው:: 2014 ከገባ ወዲህ ደግሞ ምንም ጨዋታ አላሸነፈም:: በወዳጅነት ጨዋታ በአንጎላ እና ናይጄርያ፤ በቻን ውድድር በሊቢያ፣ ኮንጎ እና ጋና፣ በሴካፋ በሱዳን እና ኬንያ የተሸነፈ ሲሆን በብራዚል ካደረጋቸው 5 የዝግጅት ጨዋታዎች ከ2 በቀር በሌሎች ተረተዋል:: ይህ ሁሉ የሚነግረን ብዙ ነገር አለ:: ቡድኑ መጀመርያውኑም በጠንካራ መሰረት ላይ አልተገነባም:: በጠንካራ ስራ የተገኙ ውጤቶች እንዳሉ ሆነው አጋጣሚ የፈጠረው ውጤትም ከግምት ውስጥ ይገባል:: ቡድኑ ከ31 አመታት በኋላ ወደ አፍሪካ መድረክ የተመለሰው ከሌሎች አመታት እጅጉን በቀለለ መንገድ መሆኑን ማስታወስ ይገባናል:: ከአፍሪካ ዋንጫው በኋላ በደበረጥ ቢሻሻልም ከአለም ዋንጫው የመጨረሻ ማጣርያ በኋላ ቡድኑ ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ወርዷል::

## የአዲሱ ፌድሬሽን እውነተኛ ፈተና

አዲሱ ፌዴሬሽን ከቻን ስኬት አልባ ጉዞ በኋላ እውነተኛ መፈተኛው ይህ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያ ነው:: የቻን ዋንጫ ሲዘጋጅ ገና በአንድ እግሩ ያልቆመው አዲሱ ፌድሬሽን ስልጣን ላይ ከወጣ አሁን አንድ አመት ሆኖታል:: የወጣቶች ውድድሮች ፣ የሊግ ውድድሮች እና አንዳንድ የፋይናንስ እና አስተዳደራዊ ስኬቶች ያስመዘገበው ፌዴሬሽን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያውን በስኬት ካልደመደመ እንደ ውድቀት ይቆጠራል::

## ስብስቡ

ከተጫዋቾቻችን ሁሉንም ብቃት መጠበቅ አስቸጋሪ ነው:: ነገር ግን በንፅፅር ይህኛው ስብስብ ለተለያዩ የጨዋታ አማራጮች ብቁ የመሆን አቅም አለው:: በየቦታው የሚገኙት ተጫዋቾች ባህርይ የተለያየ መሆን አሰልጣኙ ተለዋዋጭ እቅድ እንዲኖራቸው ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል:: በግብ ጠባቂነት ቦታ ላይ አሰልጣኙ ፈተና ውስጥ መግባታቸው አይቀርም:: በብራዚል በርካታ የመለስፍ እድል የተሰጠው ጀማል ጣሰው ቋሚ ሲሆን ቢችልም ዘንድሮ እንዳሳየው አቋም ታሪክ ጌትነት ቦታው ይገባዋል:: በትልቅ ደረጃ ስመጫወት ልምድ አልባ ቢሆንም በቅጣት እና በጉዳት የውድድር ዘመኑን ያሳለፈው ሲሳይ ባንጫ እና በጉዳት የ2006 የውድድር ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ በጉዳት ያመለጡት ጀማል ጣሰውን ማሰለፍ ምክንያታዊ ሲሆን አይችልም:: በተከላካይ ቦታ ወጣቶቹ ሳላዲን በርጊቾ እና ቶክ ጄምስ በአየር ኳስ ላይ ከሌሎች ተጫዋቾች የተሻሉ ናቸው:: የሁለቱ በተለይም የቶክ ጄምስ ፍጥነት ዝግ ያለ በመሆኑ ፈጣን እና ሰው በሰው የመቆጣጠር ችሎታው ጥሩ የሆነው ዋሊድ አታ (በቅርቡ ባጋጠመው ጉዳት ለ5 ሳምንታት ከሜዳ ስለሚርቅ በአልጄሪያ እና ማላዊ ጨዋዎች አይሰለፍም) ከሁለቱ አንዳቸውን ቢጣመር ጥሩ ሲሆን ይችል ነበር:: አዲስ መጪው ዋሊድ አታ የዘመናዊ ሊቤሮዎች ባህርይ ያለው ሲሆን ኳስን ይዞ ከአደጋ ክልል መውጣት፣ በአየር ላይ ኳስ አጥቂዎችን የመፈተንና ከሁሉም በላይ ተከላካይ ክፍሉን መምራት እና ማደራጀት ይችላል:: የደደቢቱ አክሊሉ አየነውም ከዋሊድ ጋር የሚመሳሰል ባህርይ ባለቤት ነው:: ታዳጊው አንዳርጋቸው ይላቅ እና የሀዋሳው ግርማ በቀለ ከሌሎቹ ቀድመው የመሰለፍ እድላቸው ግን ዝቅተኛ ነው:: በግራ በመስመር በኩል አበባው ቡታቆ እና ብርሃኑ ቦጋለ ለረጅም ጊዜያት በቦታው በመጫወታቸው ቦታውን ተላምደውታል:: ፈርጣማው አበባው በመከላከሉ ረገድ ጥሩ ሲሆን ረጃጅም ኳሶች እና የቆሙ ኳሶች ላይ ያለው አጠቃቀም ድንቅ ነው:: ከዝግጅት ጨዋታዎቹ አንፃር ቋሚ መሆኑ እርግጥ ቢሆንም ማጥቃት ላይ ጥሩ የሆነው ብርሃኑ ቦጋለንም ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: በቀኝ በኩል አሉላ ግርማ እና ስዩም ተስፋዬ ይገኛሉ:: ብቃታቸው ቢዋዥቅም ከነሱ የተሻሉ ተጫዋቾች በሊጉ ብዙም አይገኙም:: አሉላ ፈጣን እና ጉልበተኛ ሲሆን ማጥቃት ላይ ጥሩ ነው:: ስዩም



በጉዳት ምክኒያት በብሔራዊ ቡድኑ ያልተካተተው ዋሊድ አታ

ደግሞ በቦታው በተደጋጋሚ በመጫወቱ ለቋሚነት ተገማች ነው:: የሁለቱም ችግር የሆነው የቦታ አጠባበቅ ችግር አሰልጣኙ መሳ ካላበጁለት በመስመር ላይ አደገኛ የሆኑት አልጄርያዎች የቀኙን መስመር ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: በአማካይ መስመር ላይ የሚገኙት ተፈጥሮአዊ ተከላካይ አማካዮች አስራት መገርሳ እና ጋቶች ፓኖም ናቸው:: አዲስ እና አዳነ ፣ ናትናኤል እና ምንተስኖት ለቦታው ብቁ ሲሆኑ ቢችሉም እንደ አስራት የታክቲክ ተገዢ አይደሉም:: የአስራት በአማካይ ክፍሉ መኖር በመስመር ማጥቃትን የሚወዱት አልጄርያውያንን ለመቆጣጠር ጠቃሚ ነው:: ከተከላካይ መስመሩ ብዙም የማይርቀው አስራት ቡድኑ በሚጠቃበት ወቅት ወደኋላ በመሳብ እንደ ተጨማሪ የመሃል ተከላካይ ይጫወታል:: የመሃል ተከላካዮቹም ከመስመር ተከላካዮቹ ጋር ያላቸውን ርቀት በማጥበብ ተጠቅጥቀው ለመከላከል ያመቻቸዋል:: ቡድኑ በሚያጠቃበት ወቅትም ወደ ኋላ በመመለስ ቡድኑ በ3 ተከላካዮች እንዲጫወት ያግዛቸዋል:: ቡድኑ በ4-2-3-1 ከተጫወተ አዳነ ግርማ ወይም አዲስ ህንፃ ከአስራት ጋር መጣመር ይችላሉ::አዳነ በቡድኑ የኳስ እንቅስቃሴ ሁሉ ለመሳተፍ ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም በተደጋጋሚ ጉዳቶች ቦታው ለሚጠይቀው ብርታት ብቁ ላይሆን ይችላል:: ጋቶች የአስራት ቀጥተኛ ተተኪ ሲሆን ሌሎቹ አማካዮች ለአንድ (በ4-2-3-1) ወይም ለሁለት (4-3-3/4-4-2/4-2-2-2) የአማካይ ቦታዎች ይፎካከራሉ:: በመስመር በኩል የሜዳውን ስፋት አለመጠቀም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ድክመት ሆኖ ቀይቷል:: በአሰልጣኝ ሰውነት ዘመን በሁለቱም ክንፎች የሚጫወቱት ( ምንያህል እና ሽመልስ ) ወደ መሃል ሰብረው መግባት የሚያዘወትሩና የተጋጣሚ የመስመር ተከላካዮችን ድካም የሚቀንሱ ነበሩ:: እንደ አልጄርያ አይነት የተጠቀጠቀ የተከላካይ ክፍል ያላቸው ቡድኖችን ለማስከፈት የግድ መስመሩን በአግባቡ የሚጠቀሙ፣ የመሃል ተከላካዮችን ወደ መስመር በማውጣት የተቃራኒ የተከላካይ ክፍልን ለመበታተን ቀጥተኛ አማካዮች ያስፈልጋሉ:: በኃይሉ አሰፋ በብሄራዊ ቡድኑ አልፎ አልፎ ይህንን የሚሰራ ሲሆን የሱፍ ሳላህም ለቦታው ተመራጭ ተጫዋች ነው:: ባፌት ኤፍሬም አሻሞ ፣ ሽመልሽ በቀለን አልያም ምንያህል ተሾመን አንድ በኩል የሱፍ ወይም በኃይሉን ደግሞ በሌላኛው መስመር ቢያሰልፉ ቡድኑ ላይ መመጣጠን ሊያመጣ ይችላል:: በአጥቂ አማካይ ቦታ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ሁለት ባለ ክህሎት ተጫዋቾችን



ይዟል፡፡ ታደለ መንገሻ ግብ የሚሆኑ ኳሶችን የማቀበል እና በአብዶ ተከላካዮችን የማስከፈት ችሎታ አለው፡፡ ሽመልስ በቀለ ፍጥነት ፣ ተለዋዋጭነት እና የቴክኒክ ችሎታን አጣምሮ ይዟል፡፡ ሽመልስ በ4-4-2 ፣ ታደለ በ4-2-3-1 እና 4-3-3 ሲስተም በበተደጋጋሚ በመጫወታቸው ለአሰልጣኙ የጨዋታ እቅድ ተስማሚ ናቸው፡፡ ከግራ መስመር ወይም ከ10 ቁጥር ቦታ ላይ አደጋ መፍጠር የሚችሉ በመሆናቸው አንደኛው በመስመር አንደኛው ደግሞ በ10 ቁጥር ላይ በማሰለፍ የቡድኑን የፈጠራ ብቃት ማሳደግ ይችላሉ፡፡ በአጥቂ መስመር ሳላዲን ሰኢድ ፣ ጌታነህ ከበደ ፣ ኡመድ ኡኩሪ ፣ ፍፁም ገ/ማርያም እና ዳዋ ሁቴሳ እንደ ቅደም ተከተላቸው በአሰልጣኙ እድል ይሰጣቸዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ሳለዲን ቡድኑ የትኛውንም የጨዋታ እቅድ ቢጠቀም ነጥሮ ለመውጣት አይቸገርም፡፡ ባፊቶ በ2 አጥቂ ይጫወታሉ ተብሎ የማይታሰብ በመሆኑ ሳላዲን ከሁለት የመስመር አጥቂዎች ጋር ወይም ከ5 አማካዮች ፊት መጫወት ይችላል፡፡ ጌታነህ ከሌሎች በተለየ የሳጥን ውስጥ አጥቂ ሲሆን በአፍሪካ ዋንጫ ከመስመር እየተነሳ ሲጫወት ያሳየው አቋምን የማያመረቃ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በሁለት የመስመር አጥቂዎች ወይም ከጎኑ ተጨማሪ አጥቂ ካለ ጌታነህ ውጤታማ ይሆናል፡፡ ኡመድ ኡኩሪ በ2006 ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡ የመስመር አጥቂ ወይም ብቸኛ አጥቂ ሆኖ ቢጫወትም አይቸገርም፡፡ አሰልጣኙ የተጫዋቾቹን ባህርይ በሚገባ ከተረዱ ዋናውና ሁለተኛ የጨዋታ እቅዳቸውን ማውጣት ይችላሉ፡፡ የቀድሞውን መስወጥ ባይፈልጉ እንኳን ጥቂት መሸጋሸግ መፍጠር ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ሰውነት ቢሻው ያዘወትሩት የነበረው 4-4-2ን በዳይመንድ 4-4-2 (አስራት ሆልዲንግ አማካይ፣ በኃይሉ በቀኝ መስመር፣ ሽመልስ 10 ቁጥር እና ምንያህል ግራ መስመር) ወይም በፍላት 4-4-2 ሽመልስን ከሳላዲን ጀርባ (9 1/2ኛ አጥቂ) በማድረግ አዳነን ከአስራት ጋር አጣምረው 4-5-1 /4-2-3-1 ቅርጽ ማምጣት ይችላሉ፡፡

## ባሬቶ ጥያቄዎችን የሚመልስ ቡድን ይሰሩ ይሆን?

ስብስቡ እምብዛም አልተቀየረም፡፡ አሰልጣኙም እስካሁን ምንም የነጥብ ጨዋታ አላደረጉም፡፡ ስለዚህ ከባሬቶ ተአምር መጠበቅ አንችልም ፡፡ ነገር ግን ሰውነት ቢሻው ያስመዘገቡትን ያህል መጠበቅ ድፍረት አይደለም፡፡ ረጅም የዝግጅት ጊዜ እና በርካታ የወዳጅነት ጨዋታዎችን በማግኘታቸው የቡድናቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለመፈተሽና ቢያንስ ለአልጄርያው ጨዋታ ብቻ ለመዘጋጀት በቂ ነው፡፡ ብሄራዊ ቡድኑን ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ጨዋታ አለማሸነፋቸው ጫና ውስጥ ሲከታቸውና ለአልጄርያው ጨዋታ ያላቸውን ለመስጠት እንዲዘጋጁ ሲያደርጋቸው ይችላል፡፡ የአሰልጣኙ ከባድ የቤት ስራ ብሄራዊ ቡድኑን ካጋጠመው ከፍተኛ የውጤት ድርቅ እንዲያገግምና ዳግም በብሄራዊ ቡናችን ተስፋ ማድረግ እንድንጀምር ማድረግ ነው፡፡ ቡድኑ ያለበትን የትኩረት፣ የዲሲፕሊን (የታክቲክ እና ስነ-ምግባር) እና የወጥነት ችግር ተቀርፎ ማየት ከአልጄርያው ጨዋታ በፊት ልንመለከተው የሚገባ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡

### የእስካሁኑ ዝግጅት ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ክረምቱን በዝግጅት ተጠምዶ አሳልፏል፡፡ ዝግጅቱን በሁለት ክፍሎች ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመርያው ክፍል በሀዋሳ የተደረገው ነው፡፡ ከሐዋሳ መልስ በሉዋንዳ ከአንጎላ ብሄራዊ ቡድን ጋር ባደረጉት ጨዋታ 1-0 መሸነፋቸው የሚታወስ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል በብራዚል ያደረጉት የ21 ቀናት ቆይታ ነው፡፡ በግራናዳ ኤቨንትስ አማካኝነት ወደ ደቡብ አሜሪካዊቷ የእግርኳስ ሃገር ብራዚል አቅንተው 5 የወዳጅነት ጨዋታዎች አድርገው ተመልሰዋል፡፡ የብራዚል ቆይታቸው ከተጋጣሚዎቹ ደረጃ ዝቅ ማለትን ከግምት በማስገባት በርካቶች ትችት ቢሰነዝሩበትም በመልካም ጎንነቱም ሲነሳ ይገባል፡፡ የዝግጅት ጨዋታዎች አንዳንድ ጊዜ የማታለል አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በወዳጅነት ጨዋታዎች የተሸነፈ ቡድን ደካማ ነው ማለት አይደለም፤ ያሸነፈ ጠንካራ ነው ማለትም እንዲሁ፡፡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በዝግጅት ጨዋታዎች ድል ቢርቀውም ከአንጎላው ጨዋታ ውጪ ከጨዋታዎቹ ደረጃ አንፃር የብሄራዊ ቡድኑን አቋም ለመለካት በቂ ነው ማለት አይቻልም፡፡ የብራዚሉ ጉዞ ለዋልያዎቹ ፋይዳ ቢስ ነበር ለማለት አይቻልም፡፡ ለቡድኑ ትኩረትን እና የተጠና የዝግጅት ጊዜን አምጥቶለታል ፤ የአለም ዋንጫን በቅርቡ ያስተናገደችው ሃገር ላይ ዝግጅት ማድረግም የውድድር መንፈስን ለመፍጠር ከየትኛውም የአለም ክፍል የተሻለ ቦታ ነው፡፡



# የአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያ ዕውነታዎች


የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን እስካሁን 10 የአፍሪካ ዋንጫዎች የተካፈለ ሲሆን በማጣርያ ለአፍሪካ ያለፍንበት አጋጣሚ ሶስት ብቻ ነው፡፡ በ1957 እና 1959 ካለ ማጣርያ ለተሳተፈ በ1962 ፣ 1968 እና 1976 በአዘጋጅነት ተሳትፋለች፡፡ በ1964 በጋና አስተናጋጅነት በተካሄደው ውድድር ደግሞ ያለፈው ውድድር ቻምፒዮን በመሆኗ በቀጥታ ለውድድሩ በቅታለች፡፡ በ1966 በቱኒዚያ በተካሄደው 5ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ኢትዮጵያ በማጣርያው በኬንያ ብትሸነፍም ኬንያ ያልተገባ ተጫዋች በማሰለፏ ኢትዮጵያ በፎርፌ አልፋለች፡፡ ኢትዮጵያ ለመጀመርያ ጊዜ በማጣርያ ተጋጣሚዋን አሸንፋ ለአፍሪካ ዋንጫ የበቃችው በ1970 የሱዳን አፍሪካ ዋንጫ ላይ ነው፡፡ ዋልያዎቹ በጊዜው ታንዛንያን በድምሩ 9-1 በሆነ ውጤት አሸንፈው ለውድድሩ ቀርበዋል፡፡ በ1982 (ሊቢያ) እና 2013 (ደቡብ አፍሪካ) ጊኒ እና ሱዳንን አሸንፈው ለአፍሪካ ዋንጫ የበቁባቸው ሌሎቹ ማጣርያዎች ናቸው፡፡

## የምድብ ማጣሪያ

የአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያ በምድብ በተካሄደባቸው አመታት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አልፎ አያውቅም፡፡ ካፍ የማጣርያ ጨዋታዎች በምድብ እንዲካሄዱ የወሰነው በ1992 ሲሆን ከዛ ወዲህ ኢትዮጵያ በ8 አጋጣሚዎች ምድብ ውስጥ ገብታ ማለፍ ሳትችል ቀርታለች፡፡ በ1992፣ 94፣ 96፣ 98፣ 2004፣ 2006፣ 2008 እና 2012 በምድብ ማጣርያ የመካተት እድል ብታገኝም በአንዳቸውም የመድቡ የበላይ መሆን አልቻለችም፡

## ግብፅ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ለ1998 የቡርኪናፋሶ የአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ ከግብፅ ጋር ባደረገው የማጣርያ ጨዋታ 8-1 የተሸነፈበት ውጤት ጋና ኒጀርን 9-1 ካሸነፈችበት ጨዋታ ቀጥሎ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያ ታሪክ በትልቅነቱ 2ኛው ሽንፈት ነው፡፡



በጨዋታው ሃትሪክ የሰራው ሃዘም ኢማም

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከአልጄርያ አቻው ጋር በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያዎች ያደረጋቸው ጨዋታዎች**

ተጫወቱ - 4
ኢትዮጵያ አሸነፈች - 1
አቻ - 2
አልጄርያ አሸነፈች - 1
ኢትዮጵያ አስቆጠረች - 3
አልጄርያ አስቆጠረች - 3

ኢትዮጵያ በአጠቃላይ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣርያዎች ያደረገቻቸው ጨዋታዎች ይህንን ይመስላሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ተጫወተ - 74 | በሜዳው፡ | ተጫወተ - 39 |
| አሸነፈ - 24 | | አሸነፈ - 22 |
| አቻ - 12 | | አቻ - 9 |
| ተሸነፈ - 38 | | ተሸነፈ - 8 |
| አስቆጠረ - 76 | | አስቆጠረ - 56 |
| ተቆጠረበት - 121 | | ተቆጠረበት - 31 |

ኢትዮጵያ በታሪኳ በሰፊ ግብ ያሸነፈችው የማጣርያ ጨዋታ በኦክቶበር 1969 አዲስ አበባ ስታድየም ላይ ታንዛንያን 7-0 ያሸነፈችበት ጨዋታ ነው፡፡

ኢትዮጵያ እና አልጄርያ ለመጨረሻ ጊዜ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የተገናኙት በ1996 ሲሆን አዲስ አበባ ላይ ባደረጉት ጨዋታ 0-0 አቻ ሲለያዩ በአልጀርስ በተደረገው ጨዋታ አልጄርያ 2-0 ማሸነፍ ችላ ነበር፡፡

# የብሔራዊ ቡድኑ እውነታዎች

## ግብ የማስቆጠር ችግር



ማርያኖ ባሬቶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ሆነው ከተሾሙ በኋላ ካደረጓቸው 6 የወዳጅነት ጨዋታዎች በ4ቱ ሲሸነፍ በሁለቱ አቻ ወጥተዋል፡፡ ቡድኑ ባጠቃላይ 8 ግቦችን ያስተናገደ ሲሆን ሶስት ግቦችን ብቻ ለማስቆጠር ችሏል፡፡ በውጪ ሃገር የሚጫወቱ ተጫዋቾች ቡድኑን በመቀላቀላቸው በተለይ ግብ የማስቆጠር ችግሩ ሲቀረፍ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡



## ወጣት ቡድን...

አዲሱ የብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ማርያኖ ባሬቶ ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ ከ20 አመት በታች ብሔራዊ ቡድኑ ውስጥ መልካም እንቅስቃሴ ማሳየት የቻሉ ተጫዋቾችን ለዋናው ቡድን በመጥራት በወዳጅነት ጨዋታዎች ላይ የመሰለፍ ዕድል ሰጥተዋቸዋል፡፡ የቅዱስ ጊዮርጊሶቹ ናትናኤል፣ አንዳርጋቸው እንዲሁም የናሽናል ሲሚንቶ ክለብ ተጫዋቾች የሆኑት ዳዋ ሁጤሳ እና ማታይ ሉል ጋች ይህን ዕድል ያገኙ ተጫዋቾች ናቸው፡፡ አሠልጣኙም ወጣት ተጫዋቾቹ ላይ ባዩት ነገር ደስተኛ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡



## ቅዱስ ጊዮርጊስ

የ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ሻምፒዮኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ ለብሔራዊ ቡድኑ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተጫዋች በማስመረጥ ቀድሚያውን ይዟል፡፡ የቅዱስ ጊዮርጊስ 7 ተጫዋቾች 24 አባላት ያሉት ቡድን ውስጥ ሲካተቱ ደደቢት 5፣ ኢትዮጵያ ቡና፣ ንግድ ባንክ፣ ሐዋሳ ከነማ፣ መከላከያ፣ ዳሽን እና ናሽናል ሲሚንት ደግሞ እያንዳንዳቸው አንድ ተጫዋች ለማስመረጥ ችለዋል፡፡

## "የድል ያለህ..."




ዋሊያዎቹ በብራዚል የዝግጅት ካምፕ ወቅት ከሃገሪቱ ክለቦች ጋር ያደረጓቸውን 5 የወዳጅነት ግጥሚያዎችን ጨምሮ ካለፉት 11 ተከታታይ ጨዋታዎች በአንዱም ድል አልቀናቸውም፡፡ በ9 ሲሸነፉ 2 ጊዜ አቻ ወጥተዋል፡፡



## 2006 ዓ.ም.

ዋሊያዎቹ በ2006 ዓ.ም. ባደረጓቸው 16 ጨዋታዎች 11 ጨዋዎችን ተሸንፎ 3 ጨዋታዎች አቻ ተለያይቶ 2 ጨዋ አሸንፏል፡፡ 10 ግቦች አስቆጥረው 21 ግብ ተቆጥሮባቸዋል፡፡ ከ16 ጨዋታዎች ግብ አስቆጥረው መውጣት የቻሉትም በ6 ጨዋታዎች ላይ ብቻ ነው፡፡



## ሴካፋ 2013

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ለመጨረሻ ጊዜ ያሸነፈው ኬንያ ባዘጋጀችው የሴካፋ ዋንጫ በምድብ ጨዋታ ደቡብ ሱዳንን 2-0 ያሸነፈበት ነበር፡፡ በጨዋታው ለስዊድኑ ሲሪያንስካ የሚጫወተው የሱፍ ሳላህ እና የወላይታ ዲቻው ብሩክ ቃልቦሬ ግቦቹን ማስቆጠራቸው ይታወሳል፡፡


© SOCCER ETHIOPIA
ETHIOPIA
9
4



# አልጄሪያ

**የህዝብ ብዛት** 38.5 ሚሊየን
**ስፋት** 2,381,741 km sq.
**ዋና ከተማ** አልጀርስ
**ገንዘብ** የአልጄሪያ ዲናር
**ብሔራዊ ቋንቋ** አረብኛ

የአልጄሪያ ብሔራዊ ቡድን በአሁኑ ሰአት በአፍሪካም ሆነ በዓለም እግርኳስ ጠንካራ ከሚባሉት ቡድኖች አንዱ ነው። በተለይ በብራዚሉ የዓለም ዋንጫ ቤልጅየምን በመከተል ከምድቡ አልፎ በጥሎ ማለፉ በጀርመን ተሸንፎ ከውድድሩ እስኪወጣ ድረስ ያሳየው አቋም በብዙዎች ተደንቋል። ቤልጅየምን ለአብዛኛው የጨዋታ ክፍለ ጊዜ መምራት የቻለውና ከአዲሷ የዓለም ሻምፒዮን ጀርመን ጋር በ90 ደቂቃው አቻ መለያየት የቻለው ቡድን በእርግጥም ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥንካሬን እየጨመረ መምጣት ችሏል። የአልጄሪያ እግርኳስ ፌዴሬሽን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መከተል የጀመረው ፖሊሲም ለቡድኑ ወቅታዊ አቋም ከፍተኛውን አስተዋፅኦ አበርክቷል። ዚነዲን ዚዳን፣ ሰሚር ናስሪ እና ካሪም ቤንዜማን የመሳሰሉ ታላላቅ ተጫዋቾች ለትውልድ ሃገራቸው ፈረንሳይ በመጫወት ቢያሳልፉም በፌዴሬሽኑ ጥረት አልጄሪያዊ ዝርያ ያላቸው በርካታ ፈረንሳይ ውስጥ የተወለዱ ተጫዋቾች ለአልጄሪያ ብሔራዊ ቡድን ለመጫወት እየወሰኑ ይገኛሉ። ለዚህም በ2014ቱ የዓለም ዋንጫ ከተሳተፈው 23 ተጫዋቾችን ያቀፈ የቡድን ስብስብ ውስጥ 6ቱ ብቻ አልጄሪያ ውስጥ መወለዳቸው ግልፅ ማሳያ ነው።

በ2013ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ላይ አይቮሪ ኮስት፣ ቱኒዚያ እና ቶጎ ከነበሩበት ምድብ ውስጥ 1 ነጥብ ብቻ በማግኘት የመጨረሻውን ደረጃ ይዛ ያጠናቀቀችው አልጄሪያ ጎረቤቷ ሞሮኮ በምታዘጋጀው የአፍሪካ ዋንጫ በማለፍ ውድድሩን ለማሸነፍ አላማ አድርጋ በመስራት ላይ ትገኛለች። የቀድሞውን አሠልጣኝ ቫሂድ ሃሊልሆድዚች ተክቶ ስልጣኑን የተረከበው ክርስቲያን ጎርኩፍ በኮንትራቱ ላይ በግልፅ ከሰፈሩለት ነገሮች ውስጥ አንዱም ይህን እንዲያሳካ ነው። ከብሔራዊ ቡድኑ ጋር በሚያደርገው የመጀመሪያ ጨዋታም ኢትዮጵያን በሜዳዋ በማሸነፍ የአሠልጣኝነት ዘመኑን በመልካም ውጤት ለመጀመር ጥረት እንደሚያደርግ ይጠበቃል።

## የቀድሞ ግንኙነቶች

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 16/01/68 | ኢትዮጵያ | 3-1 | አልጄሪያ | (አዲስ አበባ) |
| 13/03/82 | አልጄሪያ | 0-0 | ኢትዮጵያ | (ቤንጋዚ - ሊቢያ) |
| 04/09/94 | ኢትዮጵያ | 0-0 | አልጄሪያ | (አዲስ አበባ) |
| 07/04/95 | አልጄሪያ | 2-0 | ኢትዮጵያ | (አልጀርስ) |

አሎምፒክ ቡድን የተደረጉ ጨዋታዎችን አይጨምርም።



## ተከላካይ


ከመሀል ተከላካይነት በተጨማሪ በአማካይ ስፍራ ላይ መጫወት የሚችለው ቡግሄራ የረጅም ጊዜ ልምድ ካላቸው የቡድኑ ተሰላፊዎች ውስጥ አንዱ ነው። ትውልድ እና ዕድገቱ በፈረንሳይ ዲጆን ከተማ ቢሆንም ከወጣት ብሔራዊ ቡድን ጀምሮ አያቱ የተወለዱባትን ሃገር አልጄሪያ በመወከል ተሰልፏል። በክለብ ደረጃም ከእንግሊዝ ዝቅተኛ ዲቪዝዮን ክለቦች አንስቶ እስከ ስኮትላንዱ ክለብ ሬንጀርስ ድረስ መጫወት የቻለ ሲሆን ከዓለም ዋንጫው መልስ አል-ፉጃራህ (Al-Fujairah) የተባለ ክለብ በመቀላቀል ወደ ኤመሬትስ (UAE) አቅንቷል።

**ማጅድ ቡግሄራ**
**ዕድሜ:** 31
**ክለብ:** አል-ፉጃራህ

## ግብ ጠባቂ

በፈረንሳይ ዋና ከተማ ፓሪስ የኮንጎ ዜጋ ከሆነ አባት እና ከአልጄሪያዊ እናት የተወለደው ምቦልሂ የማርሴይ ክለብ አካዳሚ ውጤት ነው። እንደ አብዛኞቹ የቡድን ጓደኞቹ ሁሉ ለፈረንሳይ ወጣት ቡድኖች መጫወት የቻለ ሲሆን የአልጄሪያ ብሔራዊ ቡድን ለ2010ሩ የዓለም ዋንጫ ማለፉን ተከትሎ ለአልጄሪያ ለመጫወት ወስኗል። ከማርሴይ B ቡድን እስከ ታዋቂው የቡልጋሪያ ክለብ ሲኤስኬኤ ሶፊያ (CSKA Sofia) ድረስ የበርካታ ክለቦችን ማሊያ ለብሶ መጫወት የቻለ ሲሆን በዓለም ዋንጫው ድንቅ ብቃቱን ካሳየ በኋላ ወደ አሜሪካ በማቅናት በከፍተኛ ገንዘብ ለፊላደልፊያ ዩኒየን ፈርሟል።

**ራሂስ ምቦልሂ**
**ዕድሜ:** 28
**ክለብ:** ፊላደልፊያ ዩኒየን





## አሠልጣኝ

ፈረንሳዊው የቀድሞ ስታዴ ሬኔስ እና ሎሪየንት አማካይ የቀድሞው አሠልጣኝ ቫሂድ ሃሊልሆድዚች ከስራቸው ከለቀቁ በኋላ ቡድኑን የተረከበ ሲሆን ከኢትዮጵያ ጋር የሚደረገው ጨዋታም የመጀመሪያ የነጥብ ጨዋታው ይሆናል። በፈረንሳይ ሊግ (Ligue1) የሚሳተፈውን ክለብ ሎሪየንት ከ2003 እስከ 2014 ለ12 ተከታታይ አመታት በዋና አሠልጣኝነት በመምራት ከፍተኛ ልምድ ያለው ጎርኩፍ ብሔራዊ ቡድን ሲያሰለጥን ግን አልጄሪያ የመጀመሪያው ነው። ጎርኩፍ በማጥቃት ላይ የተመሰረተ አጨዋወት በመከተል እና ወጣት ተጫዋቾችን በማሳደግ እና ለተሻለ ደረጃ በማብቃት ይታወቃል።

**ክርስቲያን ጎርኩፍ**
**ዕድሜ:** 59

## ፌዴሬሽን

**ድረገፅ:**
www.faf.org

**ምስረታ**
1962 እ.ኤ.አ.

**የፊፋ ደረጃ:**
24

**ብሔራዊ ስታዲየም:**
ሰኔ 5፣ 1962 ዓ.ም. ስታዲየም (Stade du 5 Julliet 1962)

**ታዋቂ ክለቦች:**
ኢኤስ ሴቲፍ፣ ሲኤስ ኮንስታንቲን፣ ጄኤስ ካባልዪ፣ ዩእስኤም አልጀርስ

**ከፍተኛ ግብ አግቢ:**
አብደልሻፊድ ታስፋውት (35)

**ብዙ ጨዋታ ያደረገ ተጫዋች:**
ላክህዳር ቤሎውሚ (101)



## ኮከብ ተጫዋች

በአልጄሪያ ቡድን ውስጥ ናቢል ቤንታሌብ (ቶተንሃም)፣ ሶፊያን ፌጉሊ (ቫሌንሺያ)፣ ሪያድ ማህሬዝ (ሌስተር ሲቲ)፣ ሳፊር ታይደር (ሳውዝሃምፕተን) የመሳሰሉ በእግር ኳሱ ዓለም የተሻለ ታዋቂነትን ያተረፉ ተጫዋቾች ቢኖሩም እንደ ስፖርቲንግ ሊዝበኑ ስሊማኒ ለብሔራዊ ቡድኑ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ሰው የለም።

አልጄሪያ ውስጥ ተወልደው ካደጉ ጥቂት የቡድኑ ተጫዋቾች ውስጥ አንዱ የሆነው ስሊማኒ እግርኳስ መጫወት የጀመረው በትውልድ መንደሩ ኤይን ቤኒያን ውስጥ በሚገኘው የ5ተኛ ዲቪዝዮን ክለብ ነበር። እ.ኤ.አ. በ2008 ለ3ተኛ ዲቪዝዮኑ ክለብ ጄኤስኤም ቼራጋ ክለብ ከፈረመ በኋላ በውድድር ዓመቱ 18 ግቦችን አስቆጥሮ የሀገሪቱን ታላላቅ ክለቦች ትኩረት ለመሳብ ቻለ። የዋና ከተማዋ አልጀርስ ክለብ የሆነው ሲአር ቤሉኢዝዳድም 800ሺህ የአልጄሪያ ዲናር በመክፈል ተጫዋቹን የግሉ አደረገ። ስሊማኒ በዚህ ክለብ ባሳየው እንቅስቃሴ በወቅቱ የብሔራዊ ቡድኑ አሠልጣኝ የነበሩትን ቫሂድ ሃሊልሆድዚችን በማሳመን በግንቦት 2012 ለመጀመሪያ ጊዜ ለብሔራዊ ቡድኑ ተጠራ።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ለብሔራዊ ቡድኑ ባደረጋቸው 24 ጨዋታዎች 12 ግቦችን ማስቆጠር ችሏል። ለብሔራዊ ቡድኑ እና ክለቡ ባሳየው ውጤታማ እንቅስቃሴ ምክኒያትም በ2013 ወደ ፖርቹጋሉ ስፖርቲንግ ሊዝበን ተዘዋውሯል። የ2013 የአልጄሪያ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች ተብሎ የተመረጠው ስሊማኒ በብራዚሉ የዓለም ዋንጫ ባሳየው አቋም በበርካታ ክለቦች እንዲፈለግ ስላደረገው በስፖርቲንግ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አይመስልም።

የአልጄሪያ ብሔራዊ ቡድን ከኢትዮጵያ አቻው ጋር በሚያደርገው ጨዋታም ግብ የማስቆጠሩን ሃላፊነት በዋነኛነት ስሊማኒ ላይ ጥሎታል።

**ኢስላም ስሊማኒ**
**ዕድሜ:** 26
**ክለብ:** ስፖርቲንግ ሊዝበን






# ማላዊ

**የህዝብ ብዛት** 16.5 ሚሊየን
**ስፋት** 118,484 km sq.
**ዋና ከተማ** ሊሎንግዌ
**ገንዘብ** ክዋቻ
**ብሔራዊ ቋንቋ** ቺቼዋ፣ እንግሊዘኛ

የማላዊ ብሔራዊ ቡድን በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያው ምድባችን ካሉ ቡድኖች ውስጥ ዝቅተኛ ግምት የተሰጠው እና በፊፋ ወርሃዊ የእግርኳስ ደረጃም ከኢትዮጵያ በታች ያለ ብቸኛው ቡድን ነው። ቀድሞ ነያሳላንድ ተብላ ስትጠራ የኖረችው ማላዊ ከመጀመሪያዎቹ የሴካፋ አባላት አንዷ ስትሆን የቀጠናውንም ዋንጫ ሶስት ጊዜ ለማንሳት ችላለች። ከሴካፋ በመውጣት የደቡባዊ አፍሪካ እግርኳስ ማህበርን (ኮሳፋ) ከተቀላቀለች በኋላ ሁለት ጊዜ ለኮሳፋ ዋንጫ ፍፃሜ ብትደርስም ሻምፒዮን መሆን አልቻለችም።

የማላዊ ብሔራዊ ቡድን ከተመሰረተ ጀምሮ በአህጉራዊ ውድድር ያስመዘገበው ትልቁ ውጤት በ1987 በመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ላይ ሶስተኛ በመውጣት የነሃስ ሜዳሊያ ያገኘበት ነው። ከዚህ ውጪ ለሁለት ጊዜያት ያህል (በ1984 በኮትዲቯር በተዘጋጀው የአፍሪካ ዋንጫና እንዲሁም ለ2010ሩ የአንጎላው አፍሪካ ዋንጫ) በትልቁ አህጉራዊ የእግርኳስ ውድድር ላይ ለመሳተፍ ችሎ በሁለቱም ከምድቡ አላላፈም።

እግርኳስ ወደ ማላዊ የገባው በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ስር በነበረችበት ወቅት ሲሆን በሃገሪቱ ወጣቶችም የሚያዘወትሩት ስፖርት ነው። አብዛኞቹ የማላዊ ተጫዋቾች የሚጫወቱት ቲኤምኤን የተባለ የቴሌኮም ኩባንያ ስፖንሰር በሚያደርገው የሃገራቸው ሊግ ሲሆን የተወሰኑ ተጫዋቾች የተሻለ ክፍያ ፍለጋ በጎረቤቶታቸው ደቡብ አፍሪካ እና ሞዛምቢክ ሊጎች ይጫወታሉ። ማላዊ በ2015ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ከማሊ እና ኢትዮጵያ ጋር ለምታደርጋቸው የመጀመሪያዎቹ ጨዋታዎችም 2 በሞዛምቢክ እና 6 በደቡብ አፍሪካ የሚጫወቱ ተጫዋቾችን በቡድኗ ውስጥ አካታለች። በቡድኑ ውስጥ የቲፒ ማዜምቤውን ጆሴፍ ካምዌንዶ ጨምሮ በአጠቃላይ 9 ከሀገራቸው ውጪ የሚጫወቱ ተጫዋቾች ይገኛሉ።

## የቀድሞ ግንኙነቶች

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 26/03/89 | ኢትዮጵያ | 1-1 | ማላዊ | (አዲስ አበባ) |
| 28/03/89 | ኢትዮጵያ | 1-0 | ማላዊ | (አዲስ አበባ) |
| 12/10/03 | ኢትዮጵያ | 1-3 | ማላዊ | (አዲስ አበባ) |
| 15/11/03 | ማላዊ | 0-0 | ኢትዮጵያ | (ብላንታየር) |

በሴካፋ ውድድር የተደረጉ ጨዋታዎችን አይጨምርም።



## አምበል

ከሃገሩ ቡድን ኤምቲኤል ዋንደረርስ እስከ ዴንማርክ ሱፐር ሊጉ ክለብ ኖርጅስላንድ ድረስ መጫወት የቻለው አማካይ በቡድኑ ውስጥ ልምድ ካላቸው ተጫዋቾች አንዱ ነው። እ.ኤ.አ. በ2005 ለካፕስ ዩናይትድ እየተጫወተ የዚምባብዌ ሊግ ኮከብ ተጫዋች ሆኖ መመረጥ የቻለ የመጀመሪያው የውጪ ሃገር ዜጋ ሲሆን በደቡብ አፍሪካ ኦርላንዶ ፓይሬትስ እና ቫስኮ ደጋማ እና ለሞዛምቢኩ ሊጋ-ሙኩልማና ክለብ ተጫውቶ አሳልፏል። በአሁኑ ወቅት ለኮንጎው ታላቅ ክለብ ቲፒ ማዜምቤ አባል የሆነው ካምዌንዶ የማላዊ ብሔራዊ ቡድንን ማሊያ በመልበስ ለ68 ጊዜያት ተሰልፎ 5 ግቦችን ማስቆጠር ችሏል።

**ጆሴፍ ካምዌንዶ**
**ዕድሜ፡** 27
**ክለብ፡** ቲፒ ማዜምቤ

## ግብ ጠባቂ

በሀገሩ ሊግ በምዙዙ ከተማ ለሚገኘው ሞያሌ ባራክስ ክለብ የሚጫወተው ወጣቱ በረኛ ከቤኒን ጋር በነበረው ቅድመ ማጣሪያ ሁለት የመለያ ምቶችን በማዳን ማላዊ ወደ ምድብ ማጣሪያው እንድትገባ ከፍተኛ ድርሻ ተወጥቷል። ሃራዋ የማላዊ ዋና ግብ ጠባቂ የሆነው ሲምፕሌክስ ንታራ በመጎዳቱ ምክኒያት ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ለብሔራዊ ቡድኑ የተጠራ ሲሆን የንታራ ከጉዳት አለማገገም እና በብሔራዊ ቡድኑ በተጠባባቂነት የተካተተው ግብ ጠባቂ የ45 ዓመቱ ሪቻርድ ቺፑዋ በመሆኑ ጉዳት ካላጋጠመው በቀር በቀጣዮቹ የማጣሪያ ጨዋታዎች ላይ ቋሚ ተሰላፊ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

**ማክዶናልድ ሃራዋ**
**ዕድሜ፡** 22
**ክለብ፡** ሞያሌ ባራክስ





## አሠልጣኝ

ቺሞድዚ የቀድሞው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ቶም ሴንትፊት በመስከረም ወር ከስራቸው ከለቀቁ በኋላ የተሾሙ ሲሆን በማላዊ ሊግ ለረጅም ዓመታት የማሰልጠን ልምድ ያላቸው ሲሆን የማላዊን ሊግም ለበርካታ ጊዜያት ለማንሳት ችለዋል። በብሔራዊ ቡድን ደረጃም በ2013 አሠልጣኝ የነበሩት ኪናህ ፊሪ ምክትል በመሆን መስራት ችለዋል። በአብዛኛው የውጪ ሃገር አሠልጣኝ መቅጠር የሚቀናው የማላዊ ፌዴሬሽን ስፖንሰር ለማግኘት በመቸገሩ እና ከመንግስት በቂ ድጋፍ ማግኘት ባለመቻሉ በገንዘብ እጦት ምክኒያት ቺሞድዚን እንደቀጠረ ቢታማም አሠልጣኙ ከምክትላቸው ጃክ ቻማንግዋና ጋር በመሆን መልካም ስራ እየሰሩ ይገኛሉ።

**ያንግ ቺሞድዚ**
**ዕድሜ፡** 50

## ፌዴሬሽን

**ድረገፅ:**
www.fam .mw

**ምስረታ**
1966 እ.ኤ.አ.

**የፊፋ ደረጃ:**
121

**ብሔራዊ ስታዲየም:**
ካሙዙ ብሔራዊ ስታዲየም (ብላንታየር)

**ታዋቂ ክለቦች:**
ቢግ ቡሌትስ፣ ብሉ ኢግልስ፣ ማይቲ ዋንደረርስ፣ ሞያሌ ባራክስ፣ ሲልቨር ስትራይከርስ




## ኮከብ ተጫዋች

በዴዝዳ ከተማ የተወለደው የ21 አመቱ አጥቂ ማላዊ በምታደርጋቸው ውጤታማ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ተሳታፊ ነው። ንግላንዴ በደቡብ አፍሪካው ማሜሎዲ ሰንዳውንስ እና በስፔኑ አትሌቲኮ ማድሪድ የወጣቶች አካዳሚ ውስጥ የእግርኳስ ክህሎትን የተማረ ሲሆን ላለፉት ሁለት ዓመታት ለጌታነህ ከበደ ክለብ ቢድቨስት ዊትስ ሲጫወት ቆይቶ ለሌላው የደቡብ አፍሪካ ፕሪምየር ሊግ ክለብ አያክስ ኬፕታውን በውሰት ተሰጥቷል። ለ2012 ጀምሮ ለማላዊ ብሔራዊ ቡድን መጫወት የቻለው ወጣት ከፊት አጥቂ ጀርባ በመሰለፍ በአማካይ እና አጥቂ መስመሩን የሚያገናኝ ድልድይ ይፈጥራል። ከአምበሉ ጆሴፍ ካምዌንዶ፣ ከወጣቱ የብሉ ኢግልስ አማካይ ጆን ባንዳ እና ከፊት አጥቂው ቺውኬፖ ምሶዎያ ጋር ያለው መናበብ ጥሩ ሲሆን በቀኝ ክንፍ በኩልም በመሰለፍ የመጫወት አቅም አለው።

ንግላንዴ በ2009ኙ የአፍሪካ ከ17 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ሲጫወት ባሳየው መልካም አቋም ምክንያት የደቡብ አፍሪካውን ክለብ ሰንዳውንስ ወጣት ቡድን ከተቀላቀለ በኋላ ቡድኑ ወደ ስፔኗ ዋና ከተማ ማድሪድ አቅንቶ በተሳተፈበት ኢንተርናሽናል የወጣቶች ውድድር ላይ ጥሩ እንቅስቃሴ አድርጓል። በሮቢን ብቃት የተደነቁት አትሌቲኮ ማድሪዶችም የወጣት ቡድናቸው አባል አደረጉት። ወጣቱ አንድ አመት ባልሞላ ጊዜ ከዋናው ቡድን ጋር የቅድመ ውድድር ዓመት ዝግጅት ጨዋታዎች ላይ መሰለፍ የቻለ ሲሆን ቀጣዩ ሳሙኤል ኤቶ ይሆናል ተብሎም ሲሞካሽ ነበር። ምንም እንኳን የተተነበየለት ደረጃ ላይ መድረስ ባይችልም ንግላንዴ አሁንም ቢሆን ፈጣን፣ ጥሩ የቴክኒክ ችሎታ ያለው እና ማለዊም ልዩነት ይፈጥርልኛል ብላ የምትጠብቀው ተጫዋች ነው።



**ሮቢን ንግላንዴ**
**ዕድሜ፡** 21
**ክለብ፡** አያክስ ኬፕታውን




**የብሄራዊ ቡድኑ አሰልጣኝ ማርያኖ ባሬቶ ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የመጀመርያ ጨዋታዎች የመረጧቸውን ተጫዋቾቻቸውን ስም አሳውቀዋል:: ሶከር ኢትዮጵያም የተጨዋቾቹን እና የአሰልጣኝ ስታፉን ፕሮፋይል እንዲህ ቃኝታቸዋለች::**

1. ጀማል ጣሰው:- የ2006 የውድድር ዘመን ለጀማል ጣሰው መልካም አልነበረም:: ሁለተኛውን የውድድር ዘመን አጋማሽ በጉዳት ሆስፒታል አልጋ ላይ ያሳለፈ ሲሆን በቻን እና በአለም ዋንጫ ማጣርያዎችም አሳማኝ ብቃት አሳላየም:: የሰውነት ቢሻው ቀዳሚ ተመራጭ የነበረው ጀማል የኢንተርናሽናል ጨዋታ ልምዱ እና በንፅፅር ከሌሎች በተሻለ ከተከላካዮች ጋር ጥሩ መግባባት ያለው መሆኑ፣ እንዲሁም በብራዚል የዝግጅት ጨዋታዎች የተሻለ ብቃት ማሳየቱ በባሬቶ ተመራጭ ሲያደርገው ይችላል:: የዋሊያዎቹ ምክትል አምበል ተደርጎ መሾሙ ይህን የሚያረጋግጥ ነው::

2. ታሪክ ጌትነት:- በተጠናቀቀው የውድድር ዘመን ማንነቱን በሚገባ አስመስክሯል:: አመዛኙን የውድድር ዘመን የደደቢትን ግብ በቋሚነት የጠበቀ ሲሆን 2014 ከገባ በኂላ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ጥሪ በተደጋጋሚ ደርሶታል:: የደብረዘይቱ ልጅ አሁን በቡድኑ ከሚገኙት ግብ ጠባቂዎች የተሸለ አቋም እና የጨዋታ ዝግጁነት ያለው ቢሆንም የልምድ እጥረት ለቋሚነት ሳያሳጨው ይችላል::

3. ሲሳይ ባንጫ:- ባሳለፍነው የውድድር ዘመን በቀጣት በርካታ ጨዋታዎች አምልጠውታል:: ባለፉት ጥቂት አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ከታዩ ድንቅ ግብ ጠባቂዎች አንዱ ቢሆንም በጉዳት እና ቅጣት የተጠበቀውን ያህል መሆን አልቻለም:: ከጀማል ቀጥሎ በርካታ ጨዋታ የተሰለፈው ሲሳይ ከፊቱ ከባድ ፉክክር ይጠብቀዋል::

4. አበባው ቡታቆ:- ሳለፉት 6 አመታት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን የግራውን መስመር ተቆጣጥሮት ቆይቷል:: በተጠናቀቀው የውድድር ዘመን የቅዱስ ጊዮርጊስ የቻምፒዮንነት ጉዞ ላይ ጥቂት ተሳትፎ ያደረገ ሲሆን በቀድሞ ብቃቱ ላይ የመገኘቱ ነገር አጠራጣሪ ነው:: አበባው በብራዚል የብሄራዊ ቡድኑ አምበል ሆኖ ጨዋታዎችን ያደረገ ሲሆን በ2014ቱ የዓለም ዋንጫ ማጣርያም ከሁሉም ተጨዋቾች የላቀ ጨዋታ ተሰልፏል::

5. አሉላ ግርማ:- አሉላ በጥሩ አቋም ላይ ሲገኝ ሁሉንም የማስደነቅ ችሎታ አለው:: ነገር ግን ሁልጊዜም በወጥ አቋም ለመዝለቅ ይቸገራል:: በተደጋጋሚ ለጉዳት በመጋለጡና በቦታው ለዩም ተሰፋዬ በመኖሩ ራሱን በብሄራዊ ቡድን አሳላየም:: ምናልባትም የስዩም ተስፋዬ ከቡድኑ መቀነስ ለአሉላ ትሩ አጋጣሚን የሚፈጥርለት ይሆናል:: ባሬቶ የማጥቃት ነፃነቱን ከሰጡት ድንቅ አገልግሎት የማበርከት አቅም ያለው ተጫዋች ነው::

6. ቶክ ጄምስ:- ጠንካራ፣ የተረጋጋ እና እምብዛም ጥፋት ሲፈፅም የማይታይ ተጫዋች ነው:: ከሳሳዲን በርጊቾ ጋር ሲሰለፍ ደካማ የቴክኒክ ችሎታው እና የፍጥነት ችግሩ ይሸፈንለታል:: ከቆመ ኳስ በሚሻገሩ ኳሶች ላይ አደገኛ የሆኑት አልጄርያዎችን ለመቋቋም

የቁመት መርዘም ብቻውን በቂ ባይሆንም በአካል ብቃቱ ጠንካራ የሆነው ትክ ጂምስን ማሰለፍ ከአሰልጣኙ የሚጠበቅ ነው።

7. ሳልሃዲን በርጊቾ፡- በተጠናቀቀው የውድድር ዘመን ከትንሽ ወደ ቻምፒዮን ክለብ ያደረገው ዝውውር በብዙ ረገድ ጠቅሞታል። በተመልካች ፊት የመጨዋት ስነ-ልቡናን፣ የጠንካራ ጨዋታዎች ልምድ እና እነ ደጉን የመሳሰሉ አንጋፋዎችን ልምድ ቀስሟል። ለብሄራዊ ቡድኑ አዲስ ባለመሆኑ አሁን በቡድኑ ከሚገኙት ተከላካዮች የጎላ ክፍሉን ለመምራት ተመራጭ ነው። ጠንካራ እና ወደ ፊት ወጥቶ መጫወት የሚችል ተከላካይ ነው።

8. አክሊሉ አየነው፡- አንጋፋው የደደቢት ተከላካይ በብሔራዊ ቡድን ደረጃ በብዛት ልናየው ያልቻልነው ተጫዋች ነው። በእግርኳስ ህይወቱ መጀመሪያ ላይ በአማካይ ስፍራ ላይ ይጫወት የነበረው አክሊሉ ከኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አልፎ ወደ የመን በማቅናት የዮርዳኖስ አባይ ክለብ ለሆነው አልሳቅር በመሰለፍ ሰፊ ልምድ አካብቷል። አሠልጣኝ ባሬቶ ፈጣን የሆነውን የአልጄሪያ መስመር ማጥቃት ለመቋቋም ፍጥነት ከሚጎድለው ትክ ጀምስ ይልቅ ለአክሊሉ የመሰለፍ ዕድሉን ሊሰጡት ይችላሉ።

9. ግርማ በቀለ፡- ብሔራዊ ቡድኑ ውስጥ ካሉ አዲስ ፊቶች ውስጥ አንዱ ነው። አሠልጣኙ ወደ ሐዋሳ በማቅናት የደደቢት እና ሐዋሳ ከነማን ጨዋታ ከተመለከቱ በኋላ የጠሩት ሲሆን በደቡብ አፍሪካ ክለቦች የሙከራ ጊዜ ሲያደርግ የነበረው ቢያድግልኝ ኤሊያስን ተክቶ በባሬቶ ቡድን ውስጥ ተካቷል። ዘንድሮ በፕሪምየር ሊጉ ከአዲስአበም ተስፋዬ ጋር ለሐዋሳ ከነማ ጠንካራ የተከላካይ መስመር መፍጠር የቻለ ሲሆን በብሔራዊ ቡድኑ ቋሚ ስፍራ ለማግኘት ጠንካራ ፉክክር ይጠብቀዋል።

10. ብርሃኑ ቦጋለ፡- የደደቢቱ ተከላካይ አዲሱ የብሔራዊ ቡድኑ አምበል ነው። በግራም ሆነ ቀኝ ተመሳሳሽ ቦታ የመጫወት ችሎታ ያለው ብርሃኑ በሰውነት ቢሻው ቡድን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ በተቀያሪ ወንበር ላይ ያሳለፈ ቢሆንም የባሬቶ ቋሚ 11 ውስጥ የመግባት ዕድሉ የሰፋ ነው። በጉልበቱ እና ሃይል በተቀላቀለበት አጨዋወቱ የሚታወቀው “ፋዲጋ” ከጨዋታ እንቅስቃሴው በተጨማሪ እንደ አምበልነቱ ቡድኑን በሜዳ ላይ የመምራት ሃላፊነት ተጥሎበታል።



11. አንዳርጋቸው ይሳቅ፡- በብሔራዊ ሊግ ከሚጫወተው የድሬዳዋ ክለብ ናሽናል ሲሚንት የተገኘው ይህ ወጣት ከ20 ዓመት በታች ቡድኑ ከሲሼልስ እና ደቡብ አፍሪካ አቻው ጋር ባደረጋቸው የአፍሪካ ወጣቶች ዋንጫ ማጣሪያዎች ባሳየው የተሻለ አቋም ምክኒያት በብሔራዊ ቡድኑ ሊጠራ ችሏል። ወጣት ተጫዋቾችን በማሳደግ ለተሻለ ደረጃ የማብቃት ልምድ ያላቸው ባሬቶ የወደፊቱ ብሔራዊ ቡድን መሠረት ይሆናሉ በማለት ከመረጧቸው ተጫዋቾች አንዱ ነው።

12. አስራት መገርሳ፡- በዳሽን ቅዝት የሆነ የውድድር ዘመን አሳልፏል። በብሄራዊ ቡድኑ የአለም ዋንጫ ማጣርያ ጨዋታዎች በተለይም ከናይጄርያ ጋር ባሳየው አቋም ከበርካቶች የሙገሳ ቃላት ከጎረፉለት በኋላ የቀድሞ አቋሙ ላይ መገኘት አልቻለም። በወጣቱ ናትናኤል ዘለቀ ቦታውን የተነጠቀ ይመስላል። የዳሽን ቢራው አማካይ አሁንም ቢሆን የጨዋታ ፍጥነት የመቆጣጠር፣ ኳስ የማደራጀት እና እንደተጨማሪ ተከላካይ ሆኖ መጫወት ላይ ድንቅ ነው። የፍጥነቱ ዝግ ማለት በቦታ አጠባበቅ ላይ ደካማ ለሆነው ቡድን መመጣጠንን ሊያመጣ ይችላል።

13. አዳነ ግርማ፡- አሁን በቡድኑ ውስጥ ከሚገኙ ተጫዋቾች አንጋፋው ሆኗል። በተለያዩ



ሚናዎች እንዲጫወት መደረጉ እየጎዳው መምጣቱ በግልፅ እየታየ መጥቷል፡፡ ባለፉት ሁለት አመታት ወደ አማካይነቱ በመመለሱ አጥቂ ሆኖ ይጫወታል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ የከፍተኛ ልምድ ባለቤት በመሆኑ በሜዳም ሆነ ከሜዳ ውጪ የዋልያዎቹ መሪ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

14. *አዲስ ህንፃ*፡- የአህሊ ሼንዲው ኮከብ ወደ ሱዳን ካመራ ወዲህ በብሄራዊ ቡድን ጨዋታዎች የተመለከትነው ለጥቂት ጊዜያት ነው፡፡ የሱዳን አቋሙን ብዙዎች ባለመመልከታቸው የአዲስን ብቃት መገመት አስቸጋሪ ነው፡፡ ቢሆንም እረፍት የለሽ እና በቅብብል ላይ ለተመሰረተ እግርኳስ ምቹ መሆኑ አሰልጣኙን ሊያሳምን ይችላል፡፡

15. *ምንያህል ተሸመ*፡- ምንያህል የ2006 አቋሙ አንፀባራቂ አይደለም፡፡ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቋሚ አሰላለፍ ሰብሮ ለመግባት የተቸገረ ሲሆን በኢትዮጵያ የዝግጅት ጨዋታዎች ላይም ተሳትፎ አላደረገም፡፡ በሁለቱ መስመሮች እና በአጥቂ አማካይነት መጫወት የሚችለው ምንያህል አሰልጣኝ ባሬቶ ቀጥተኛ አጨዋወት የሚመርጡ ከሆነ በአሰልጣኙ እምነት ላያገኝ ይችላል፡፡

16. *ሽመልስ በቀለ*፡- የማጥቃት አእምሮ ያለው፣ ፈጣን እና ተከላካዮችን በቀላሉ ማለፍ የሚችል ባለተሰጥኦ አማካይ ነው፡፡ አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው አባክነዋቸዋል ከሚባሉት ተጫዋቾች አንዱ የሆነው ሽመልስ በሰውነት 4-4-2 አሰላለፍ ውስጥ የቀኝ መስመሩን ይዞ ሲጫወት እናውቀዋለን፡፡ ክለብ አልባ መሆኑ ለጨዋታ ብቁ ላያደርገው ቢችልም ባሬቶ በቀድሞው ቡድን ላይ ለውጥ ማድረግ ካልፈለጉ የሽመልስ ቋሚነት የተረጋገጠ ነው፡፡ ባሬቶ የሽመልስን ብቃት አውጥተው ለመጠቀም ካሰቡ 4-4-2 ዳይመንድ አልያም 4-2-3-1 ለሽመልስ ይስማማዋል፡፡ በ4-4-1-1 አሰላለፍ ከብቸኛው አጥቂ ጀርባ ቢሰለፍም ድንቅ አገልግሎት ሊያበረክት ይችላል፡፡

17. *ኤፍሬም አሻሞ*፡- አሰልጣኙ በመስመር አጥቂዎች መሰለፍ ከፈለጉ ትክክለኛው ምርጫ ነው፡፡ ከመስመር እየተነሳ ከአጥቂዎች የማይተናነስ ግብ የሚያስቆጥረው አዲሱ የንግድ ባንክ ተጫዋች አሰልጣኙ የፖርቱጋላዊያን ዜቤ የሆነውን ፈጣን የመስመር አጨዋወት ለመተግበር የኤፍሬም አሻሞ የጨዋታ ባህርይ ሊገፋፋቸው ይችላል፡፡

18. *ታደለ መንገሻ*፡- የአስደናቂ ክህሎት ባለቤት ነው፡፡ ከግራ መስመር ወይም ከመሃል እየተነሳ አደጋ መፍጠር ይችላል፡፡ በተጠናቀቀው የውድድር ዘመን ብቸኛ ድክመቱ የነበረው የግብ ማስቆጠር ችግሩን የቀረፈ ሲሆን የግብ እድሎችን በመፍጠር በኩል ከሁሉም የላቀው ነው፡፡ በ4-2-3-1 ወይም በ4-4-2 ዳይመንድ ቢሰለፍ የበለጠ ይጎላል፡፡ በዳጋፊዎች ከሚወደደው ሽመልስ በቀለ ጋር የሚያደርገው ፉክክር ለአሰልጣኙ ትልቅ የቤት ስራ ይሆንባቸዋል፡፡

19. *ምንተስኖት አዳነ*፡- ከክቡር አቶ ይድነቃቸው ተሰማ መታሰቢያ ውድድር የተገኘው የተከላካያ አማካይ የተሳካ የሚባል የውድድር ዘመን አሳልፏል፡፡ በቅዱስ ጊዮርጊስ የሻምፒዮንነት ጉዞ በሁለቱ ሆላንዳውያን አሠልጣኞች ስር በቂ የመሰለፍ ዕድል ያገኘ ሲሆን ብሔራዊ ቡድኑ በሴካፋ እና በደቡብ አፍሪካው የቻን ውድድር ባደረጋቸው ጨዋታዎችም ለመሰለፍ ችሏል፡፡ ፍጥነቱ፣ ቅልጥፍናው እና ኳስ የመንጠቅ ችሎታው ጥሩ የሆነው ምንተስኖት በረጅም ኳስ የመጣል ልምድ እምብዛም ስለሌለው በባሬቶ ቡድን ውስጥ ቦታ ሊያጣ ይችላል፡፡

20. *ናትናኤል ዘለቀ*፡- የቅዱስ ጊዮርጊሱ ወጣት ቡድን አማካይ በባሬቶ ትልቅ ተስፋ ከተጣለባቸው ተጫዋቾች አንዱ ነው፡፡ በጥቂት የፕሪምየር ሊግ ጨዋታዎች ብቻ ለጊዮርጊስ ዋናው ቡድን መሰለፍ የቻለው ናትናኤል በአልጄሪያው ጨዋታ ግን መሰለፍ ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ በልምምድ ወቅት አስገራሚ ብቃት በማሳየት ባሬቶን ማሳመን በመቻሉ አስራት መገርሳን የመሰለ አንጋፋ ተጫዋች ሊያስቀምጥ እንደሚችልም እተነገረለት ይገኛል፡፡ ናትናኤል ጥሩ ተክለ ሰውነት እና ረጅም ኳሶችን የማቀበል ችሎታ ያለው ሲሆን ወጣት በመሆኑም ለቀጣይ ዓመታት ብሔራዊ ቡድኑን ማገልገል ይችላል፡፡

21. *የሱፍ ሳላህ*፡- ለስዊድኑ ሲሪያንስካ የሚጫወተው የሱፍ በተለይ ከ2013ቱ የአፍሪካ ዋንጫ በፊት ታንዛኒያ ጋር በተደረገው የወዳጅነት ጨዋታ ድንቅ አቋም ቢያሳይም ከዚያ በኋላ በሴካፋ እንጂ በዋናው ቡድን ውስጥ ለበቂ ጊዜያት መሰለፍ አልቻለም፡፡ እውነተኛ የመስመር ተጫዋች ሲሆን ለባሬቶ የ4-3-3 አሰላለፍ ትክክለኛ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡



22. ሳላዲን ሰኢድ፡- የብሄራዊ ቡድኑ ኮከብ ነው፡፡ የአል-አህሊው የግብ አዳኝ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ውስጥ ከተካተተ በተጠባባቂ ወንበር ላይ ማስቀመጥ የማይታሰብ ነው፡፡ ሳላ በየትኛውም የጨዋታ ሲስተም ውስጥ ነጥሮ የመውጣት ባህርይ ባለቤት መሆኑ ለአሰልጣኙ በርካታ አማራጭ ይፈጥርላቸዋል፡፡ በ4-5-1 በብቸኛ አጥቂነት፣ በ4-4-2 ከተጨማሪ አጥቂ ጋር እንዲሁም በ4-3-3 ከ2 የመስመር አጥቂዎች ጋር ቢጫወት አኩል ግልጋሎት ማበርከት ይችላል፡፡ ጉዳት ከጨዋታ ውጪ ካላደረገው በጨዋታዎች ላይ ልዩነት መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡

23. ኡመድ ኡኩሪ፡- በሰሜን አፍሪካዊቷ ሃገር አዲስ ህይወት ከመጀመሩ በፊት የፕሪሚየር ሊጉን ኮከብ ተጫዋችነት እና ግብ አግቢነት ክብር ደርቦ ወስዷል፡፡ ከሌሎች አጥቂዎች ጋር ሲነፃፀር የተሟላ አጥቂ ነው ለማለት ባይቻልም የተዘጋ የተከላይ መስመርን በጠንካራ ምቶች የማስከፈት እንዲሁም ከተከላካይ ጀርባ በሚያደርገው ሩጫ ለአሰልጣኙ ተጨማሪ የታክቲክ አማራጭ ይፈጥርላቸዋል፡፡

24. ጌታነህ ከበደ፡- በቅርብ ጊዜያት ከታዩ አጥቂዎች የጌታነህን ያህል የግብ ማስቆጠር ችሎታን የታደሉ ተጫዋቾ የሉም፡፡ በጉዳት በርካታ ጨዋታዎች ባይሰለፍም በደደቢት፣ ቢድቬትስ ዊትስ እና ብሄራዊ ቡድኑ የተጫወተውን ደቂቃ እና ያስቆጠረውን ግብ ከግምት ካስገባን ጌታነህን ከቋሚ አሰላለፍ ማውጣት የማይታሰብ ነው፡፡ ከጎኑ ተጨማሪ አጥቂ ከተሰለፈ አልያም በሁለት ክንፎች የመስመር አጥቂዎች ካሉ ግብ ለማስቆጠር አይቸገርም፡፡ ጨዋታዎቹ ጠንካራ በመሆናቸው አሰልጣኙ በአንድ አጥቂ መጫወትን ከመረጡ ጌታነህ ሰለባ መሆኑ አይቀርም፡፡

25. ዳዋ ሁጤሳ፡- ከድሬዳዋው ናሽናል ሲሚንት የተገኘው ሌላው የወጣት ብሔራዊ ቡድኑ ተጫዋች ሲሆን ባፌቶ ከአንጎላ ጋር በተደረገው የወዳጅነት ጨዋታ እና በቡድኑ የብራዚል ቆይታ ወቅት የመሰለፍ ዕድል ተሰጥቶታል፡፡ በክረምቱ የዝውውር ምኮት ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለመግባት እንደተቃረበ የሚነገርለት ዳዋ ፍጥነቱ እና ተከላካዩን ማስጨነቅ ችሎታው ጥሩ ቢሆንም በቀጣዮቹ ጨዋታዎች የሚሰለፍ አይመስልም፡፡ ዳዋ እስካሁን በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ እንኳን መጫወት ባለመቻሉ በቂ ልምድ ይጎድለዋል፤ እነ ሳልሃዲን፣ ጌታነህ እና ኡመድን ማስቀመጥ ይችላል ተብሎም አይጠበቅም፡፡



ጀማል ጣሰው
(መከላከያ)
ግብ ጠባቂ



ሲሳይ ባንጫ
(ደደቢት)
ግብ ጠባቂ



ታሪክ ጌትነት
(ደደቢት)
ግብ ጠባቂ




አበባው ቡጣቆ
(ቅ/ጊዮርጊስ)
ተከላካይ



አሉላ ግርማ
(ቅ/ጊዮርጊስ)
ተከላካይ



ቶክ ጀምስ
(ኢ/ቡና)
ተከላካይ




ሳልሃዲን በርጌቾ
(ቅ/ጊዮርጊስ)
ተከላካይ



አክሊሉ አየነው
(ደደቢት)
ተከላካይ



ግርማ በቀለ
(ሐዋሳ ከነማ)
ተከላካይ



ብርሃኑ ቦጋለ
(ደደቢት)
ተከላካይ



አንዳርጋቸው ይሳቅ
(ናሽናል ሲሚንት)
ተከላካይ



አስራት መገርሳ
(ዳሽን ቢራ)
አማካይ



አዳነ ግርማ
(ቅ/ጊዮርጊስ)
አማካይ



አዲስ ህንፃ
(አህሊ ሸንዲ)
አማካይ



ምንያህል ተሾመ
(ቅ/ጊዮርጊስ)
አማካይ



ሽመልስ በቀለ
(ክለብ ዮስዉም)
አማካይ



ኤፍሬም አሻሞ
(ንግድ ባንክ)
አማካይ



ታደለ መንገሻ
(ደደቢት)
አማካይ



ምንተስኖት አዳነ
(ቅ/ጊዮርጊስ)
አማካይ



ናትናኤል ዘለቀ
(ቅ/ጊዮርጊስ)
አማካይ





ዩሱፍ ሳላህ
(ሲፊያንስካ)
አማካይ



ሳልሃዲን ሰይድ
(አል አህሊ)
አጥቂ



ዑመድ ዑክሪ
(ኢ/አሌክሳንድሪያ)
አጥቂ



ጌታነህ ከበደ
(ቢድቨስት ዊትስ)
አጥቂ